# ስብስብ ግጥሞች

(ፏራ እልባ ጎጆዎች፣ የሳት ዳር ሀሳቦች እና
ሌሎች አዳዲስ ግጥሞች)

በዕውቀቱ ስዩም

t.me/etbookstore



# መክፈቻ

## እኔ እና ቤቴ

ግጥም የሕያው ስሜቶች ምስክርነት እንደ ኾነ እናምናለን፤ ምናባዊ መገለጥ እንደ ኾነ እናምናለን፤ ለአያቶቻችን ከመለኮት ጋራ የሚያገናኝ መሰላል፤ ለአባቶቻችን የአብዮትን ሰይፍ የሚስል ሞረድ፤ ለእኛ ፍለጋ (ኀሠሣ) መኾኑን እናምናለን፤ ያልተንዛዛ ልቅሶ፣ ያልቆረፈደ ተረብ፣ ያልተዝረከረከ ፍልስፍና መኾኑን እናምናለን፤ ለገጣሚው ብቻ የተሰጠ መክሊት እንደ ኾነም እናምናለን።

ገጣሚም ያላረገዘውን የማያምጥ፣ ያላማጠውን የማይወልድ፣ ያልወለደውን የእኔ ብሎ የማይጠራ እንደ ኾነ እናምናለን፤ በጭብጨባ ብዛት የማይለመልም፣ በእርግማን ብዛት የማይከስም እንደ ኾነ እናምናለን። ከሁሉም በላይ ለዘመዶቹ (ለሰው ልጆች) የሚገደው ልባም እንደ ኾነ እናምናለን። አምነንም እንጽፋለን ...

# በላዔ ሰብእ

ከፍልስጤ በፊት ቆረብኩኝ በእምዬ
ነጭ ደሟን ጠጣኹት ወተቷ ነው ብዬ
እውነት! እውነት! እውነት!
ከናቱ ዕቅፍ ወርዶ ምድርን እስኪቆፍር
ሰው በላዔሰብ ነው በደም የሚወፍር።

# ይኽው እንደ ዋዛ

ይኽው እንደ ዋዛ!
ተራሮች ፈለሱ
ኮረብታዎች ሄዱ
ውሆች ተወሰዱ
ማነን? ብንላቸው
ፈጽመው ረስተን
በኛ ተሰይመው
ዛሬ'ኛን ስም ነሱን።

ይኸው እንደዋዛ!
ባለበት እንዲገኝ
መሬት መች ታመነ
መሀል የነበረው
ዳርቻችን ኾነ።

ይኸው እንደዋዛ!
አራሹ ሳይለግም
ሳይሳሳ ደመና
ሀሳዊን ድርቅ መታት
ዘር መውደቂያ አጣና።

*ሀሳዊ- ኑሮ

# የፍቅር ቀዶ ጥገና

በሰው ልጅ ልብ ውስጥ፣ ባ'ዳም ዘር ስብእና
ያ'ውሬነት ቅጥያ መቼ ይጠፋና
ቀንድ፣ ጭራ፣ ክራንቻ ኩንቢና ሸሆና
ልቤ ይህን አምኖ ማከዳን መስለ
ወደ ፍቅር ገብቶ ቅጥያውን ጣለ።

# የይቅርታ መሐልይ

ማነው የፈለገኝ?
በማይነጋ ሌሊት
በማይመሽ ቀን መሀል
ተዘርሬ ስገኝ::
ከተውሽኝ በኋላ 'ርቃን ቀርታ ነፍሴ
እንኳን ከሰው ዐውድ ተነጠልሁ ከራሴ::

*　　*　　*

ተመልሼ ልምጣ ተመልሰሽ ነዪ
ልጣል ምሰሶዬን ማገርሽን ጣዪ
አዲስ ቤት መገንባት ዛሬ መች ይደላል
ለምደው ወደተዉት መመለስ ይቀላል::

*　　*　　*

ካሳ ባልክልሽ ቁና ጤፍ ሰፍሬ
ባዶ እጄን አልቆምም ከደጅሽ ደፍሬ
ጽንፍ የለሽ ይቅርታን ውሰጅ ከከንፈሬ::

# አቤል እና ቃየን

በሰላም ሰፍሮ ሳለ 'ምድር' ባላት ባፉ
ጥዳኙ ሲመታ፣ አቤል ሚስኪኒቱ ወፉ
ቃየን ጠጠር ነበር፣ ለባለወንጭፉ።

## የ'ኔ ነጻ ፈቃድ

የ'ኔ ነጻ ፈቃድ
ምን ኩሬ ቢመስልም
የረጋ ከጉድጓድ
ድንገት ሲወርድበት
ደራሽ ውኃ ኾኖ
የሌሎች ተጽዕኖ
ኀይልና ማዕርግ
ሳይፈልግ ይጓዛል
በማይወደው ፈለግ::

# ሐበሻው ፑሽኪን

ወንጀለኛ ቢኾን ዓለም አሸባሪ
አራጅ ቢኾን ኖሮ ቤት ንብረት መዝባሪ
ፑሽኪን አሌክሳንደር
"ባያቱ ሐበሻ ነው" መች እንለው ነበር!!

# መልክአ ሕይወት

ጧልትን ከፈገግታ

ሣቅን ከፌዝ ጋራ

ባንድ ላይ ቀይጠን

አቅልመን በጥብጠን

በሐዘን ባሕር ላይ፣ ብናንቆረቁርም

ባሕሩ ሰፊ ነው፣ መልኩን አይቀይርም።

## አንሺ እና ወዳቂ

ተዘርሮ አየኙት
ቀርቤ አነሣኙት
እሱ ግን ተከፋ
ቅስሙ ተሰበረ
አብሬው ባልወድቅ
ሳይጽናና ቀረ።



## አዳም እና ሚስቱ

አዳም የትላንቱ
የጥንት የጠዋቱ
ሳይለፋ ሳይታክት ተኝቶ ባደረ
ውኃ አጣጭ አቻውን ተጎኑ ተቸረ፤
ይብላኝ ላ'ሁኑ አዳም ለታካች ምስኪኑ
ምነው በተኛና በሸሸሁ ተጎኑ
ለምትል ሔዋኑ።

# ዘመን ሲታደስ

እኛ'ኮ ለዘመን

ክንፎቹ አይደለንም

ሰንኮፍ ነን ለገላው

ቢታደስ ቁጥር፣ የምንቀር ከኋላው።



# የበረሓ ጠኔ

በረሓ ላይ ቆሜ ጠኔ ሲያደባየኝ

ቆሞ ሲያመሰኳ ግዙፍ ግመል ታየኝ፤

ሰውነቴ ደክሞ ሆዴ እየተራበ

እጄ መጣፍ ገልጦ ቃሉን አነበበ

«ካመሰኳ ብላው» ይላል የፊተኛው

«ሸኾናው ክፍት ይኹን» ይላል ሁለተኛው፤

የፊተኛው ት'ዛዝ በፍጹም ተሳክቷል

ግመሉን አየኹት ቅጠል ያመሰኳል

ሸኾናውም ቢኾን

አሸዋው ሸፍኖት

ጥልቅ አቧራ ውጦት

ካ'ይኔ ቢሰወርም

ክፍት እንደ ኾነ ግን አልጠራጠርም።

# ኀሠሣ ሥጋ

እልፍ ከሲታዎች ቀጥነው የሞገጉ
«ሥጋችን የት ሄደ?» ብለው ሲፈልጉ
በየሸንተረሩ፣ በየጥጋጥጉ
አሥሠው አሥሠው በምድር በሰማይ
አገኙት ቦርጭ ኾኖ ባ'ንድ ሰው ገላ ላይ፡፡



# ተማፅ'ኖ

አቤቱ!
እህል ውኃ ሚሸሽብን
ለባዊነት አመለጠን
ሆድ የሚያኽል ልብ ስጠን
በሆዳችን ልክ ሥራው
የልባችንን መጠን፡፡

# የሞት ንቀት

ሞት የፈለገ'ንደኹ
አንተን ለማዋረድ
እኔን ግን ለማክበር
ነፍሴን ግብ አድርጎ
ወደ ቤቴ ሲበር
ያኔ እግሬ መንገዱን
ያገኳኳል ያንተን በር።



# ሞኝ ፍቅር

ለ'ሱ
ሰው ብቻ አይደለችም
ጠፈር ናት ባ'ካሏ
መሬት ናት በነፍሷ
ዕድሜ ልኩን ቢሮጥ
አያመልጥም ከ'ሷ።

# ሹክሹክታዋ

እምቢልታው ሰልችቶኝ
ክራሩ አስጠልቶኝ
በዋሽንት በርግጌ
ባ'ታሞ ደንቱሬ
ከዜማ ከልሳን
ስናር ተቃቅሬ
ባ'ርምሞ ስጸልይ
ባ'ርምሞዬ ስተኝ
ሹክሹክታዋን ሳክ
ከድምፅ ሊያስታርቀኝ
እያልቅበት ታምር
እያልቅበት ድኒን
ጆሮ እንደ ጉሮሮ
ሹክሹክታ እንደ ክኒን
አድርጎ እያስማማ
ተውሳኬን ነቀለው
ድምፅዋን እያሰማ።።



# መሄጃ የታለ?

በመዳህ እያለን
መሄድ ሳንችል ገና
መንገድ ሞልቶ ነበር በሽ ነበር ጎዳና
ዛሬ መሄድ ሲያምረን እግሮቻችን ጸንተው
መሄጃ ቸገረን መንገዶቹ ጠፍተው።።

# ኗሪ አልባ ጎጆዎች

**አያቶች!**
**በባዶ መስክ ተመራምረው**
**ጥበባቸውን**
**ዕድሜያቸውን**
**ገብረው**
**የጎጆ ንድፍ ሲያበጁ**
**አረጁ**
**ዘመናቸውን ፈጁ**

**አባቶች!**
**መላ ዘመናቸውን**
**ጎጆ በመቀለስ አሳለፉ**
**ሳይኖሩበት አለፉ**

**ልጆች!**
**ጎጆውን ለመውረስ ሳይከጅሉ**
**እንዲህ አሉ**
**«ያባቶቻችን ጎጆ**
**ይኹን ባዶ ይኹን እና**
**በኛ ቁመት**
**በኛ መጠን**
**አልተቀለሰምና።»**



# አዳም እና ጥበቡ

በመጀመሪያ አዳም ሳተ
ከገነትም ተጎተተ
አዳም ከገነት ሲባረር
እነሆ ርቃኑን ነበር
ብርዱ፣ ውርጩ አንዘፈዘፈው፣ ዶፉ ጠሉ ወረደበት
ያንዠረገገውን አይተው አዕዋፍ አራዊት ሣቁበት
ይኼኔ አዳም ተማረረ
ተማረረና ተመራመረ
ተመራምሮም አልቀረ
ጋቢ መሥራት ጀመረ፤
ጅማሬውን ወደደ
ተጀምሮ እስቲፈጠም
የዕድሜውን ግማሽ ወሰደ፤
ያሳዝናል!
ጋቢውን ጨርሶ ሲቋጭ ገላው ብርዱን ለመደ።

## ወደ ምንም የሚያደርሰው መንገድ

ቸኳይ የሚመስለው
ፈጣን የሚመስለው
በውልውል መኪና
በፋሽን መጫሚያ
ወይም በባዶ እግሩ
ሸው እልም የሚለው
ይኼ ሁሉ ምሁር፣ ይኼ ሁሉ ማይም
መንገዱን የሞላው ከታችም ከላይም
ሲመላለስ እንጂ ሲደርስ አይታይም።



## ብታውቂ !

ስትሥቂ!
ጠፈርን እንደም;ታደምቂ
መንፈስን ካዚም እስራት
እንደም;ታላቅቂ
ብታውቂ!
ስትስሚ!
አጥንት እንደም;ታለመልሚ
;ታማሚ ልብ እንደም;ታክሚ

ብታውቂ!

ስታወሪ!
ዱዳ እንደም;ታናግሪ
መነኩሴውን ከሰባኤ
ፈላስፋውን ከጉባኤ
እንደምትጠሪ

ብታውቂ!

እንኳንስ በ'ኔ ልትሥቂ
ከራስሽ ,ጋራ ፍቅር ይዞሽ
አይሽ ነበር ስትማቅቂ !!!

# ጥጡ እና ፈታይዋ

ባበባነት ወቅቱ
ጥጥ ነኝ ብሎ ቀርቧት
ፈታይ ኾና ቀርባው
ከሥሩ ፈንቅላው
ከንበጡ ፈልፍላው
ከማ'ረጉ አውርዳ
መሬት አስተኝታው
በፈገግታ በትር
በሣቅ ማዳወሪያ
ቀኑን ሙሉ ወቅታው
በድምጧ መንደፊያ
ባ'ይኗ መዳመጫ
ከፍሬው ለይታው
ለካ እሱም ተረትቶ
ሰውነቱን ትቶ
(አምኖ ጥጥነቱን)
መዳፏ ሥር ገብቶ፣
ድድር ገላው ሣሥቶ
ጥብቅ ጉልበቱ ላልቶ
ኾኖላት ባዘቶ



በስሜት እንዝርቷ
ታብቶላት ዐሥራው
በራቁት ጭኗ ላይ
አሽከርክራ አሹራው
ሲወፍር አቅጥናው
ሲረግብ አከርራው
ሲያስኛት ልቃቂት
ሲሻት ቀለም አ'ርጋው
ለካ እሱም ተረቶ
ሰውነቱን ትቶ
ጥጥነቱን አምኖ
እንዳደረገችው እንዳስኛት ኾኖ
መለወጡን እንኳ ሳያስብ ላ'ንድ አፍታ
ከጥጥነት ልቆ ኾኗት ቀጭን ኩታ
ቀን ቀን ለውበቷ
ማታ ለሙቀቷ
ሲኾን ሰነባብቶ
ዕድፍ እና ትቢያ ከገላዋ አንሥቶ
ጸዐዳው አካሉ እያደር ጨቅይቶ
እሷ ሳትለወጥ
እሱ ነትቦ አርጅቶ
ተሽቀንጥሮ ቀረ ኾነና ቡትቶ
በሌላ ጸዐዳ ኩታ ተተክቶ።።

## ጎሠሣ ሰላም

ማጭድ ይኾነን ዘንድ፣ ምኒሽር ቀለጠ
ዳሩ ብረት'ንጂ፣ ልብ አልተሰጠ
ለማር ያልነው ስለት፣ እልፍ እንገት ቀረጠ።



## ፍጻሜ ዓለም

ያዳም ልጆች ክፋት
በዝቶ ሲያስጨንቃት
ልክ እንደ ቅሪላ አብጣ አብጣ ሲበቃት
ፈንድታ ታርፋለች ብለን ስንጠብቃት
ዓለም አለሁ ብላ እኛን አዘናግታ
እንደ እንኳር በረዶ
እለቶች ቀስ በቀስ
እጃችን ላይ ሟሙታ።

# የመጻተኛው ዝማሬ

ሰው ቤቱን ሲያቋቁም
ቁሳቁስ ሲለቅም
ጥሪት ሲያጠራቅም
መጻተኛው እኔ
መሄድ ያስለመደኝ
ገላ ኮተት ኾኖ፣ ይኖራል ሲከብደኝ።

## ጣይ እና አንሺ

ደሞዙን ቢጥል
አንሥተው ጠጡበት
ባርኔጣውን ቢጥል
ወስደው ደመቁበት
ከዘራውን ቢጥል
ተመረኮዙበት
በሄደበት ሁሉ
እየተከተሉ
በጣለው ሲያጌጡ
በጣለው ሲያተርፉ
ራሱን ሲጥል ግን
አይተውት አለፉ።

# መልክአ እናት

ሰላም ለኪ እናታችን
ባለሽበት እንዳለሽ
ከዘመኑ ሴቶች ተለይተሽ
አንቺ የተባረክሽ ነሽ
ሰላም ለዐይኖችሽ
ከጭስ ጋራ ለሚሟገቱ
ከእንቅልፍ ጋራ ለተፋቱ
ተቅበዝባዥ ፍጡር ኾኜ ኑሮዬን ከምገፋ
ምነው እንባሽን በኾንኩ
ካ'ይኖችሽ ሥር እንዳልጠፋ።
ሰላም ለከንፈሮችሽ
ትላንት ለማውቃቸው
ዛሬ ለምናፍቃቸው
ውዳሴ ክብር ምርቃት
ጭብጨባ ሙገሳ ሽልማት በተረፈበት ቀዬ
ምነው ያ'ንቺን እርግማን - ይናፍቃል ጆሮዬ
ከሌሎች ውዳሴና ክብር እልፍ ጊዜ የተሻለ
ለካ በ'ርግማንሽ ውስጥ እናትነትሽ አለ።
ሰላም ለጣቶችሽ
ለሰዎች የቀረቡ፣ ከራስሽ ግን የራቁ

መስጠት መስገስ እንጂ መቀበልን ለማያውቁ
ሰላም ስኪ!
ባለሽበት እንዳለሽ።

# የመጻተኛው ኑዛዜ

ካ‘ገር ጫፍ እስከ ጫፍ በጥላህ ከልለህ
ተራራው የ‘ኔ ነው ለምን ትለኛለህ?
ወንዙ ድርሻዬ ነው ለምን ትለኛለህ?
እንኳንስ መሬቱ አንተም ያ‘ንተ አይደለህ

* * *

እኔ መጻተኛ አንተ ኗሪ ነኝ ባይ
እኔ እግሬን ስከተል ርስትህን ስታይ
ስቀርብህ ገፋኸኝ ስትገፋኝ ቦታ አጣኹ
ድንኳን ብትተክል፤ ነፋስ ኾኜ መጣኹ

* * *

ያ‘ባትህ ያ‘ባቴ
ጠበኛ ስማቸው
ጠበኛ ሕልማቸው
በሕይወት ተጣሉ፤ ታረቁ ባ‘ፅማቸው
ባ‘ፈር ተቃቃሩ አፈር አስማማቸው
በዙሪያቸው በቅሎ ከቧቸው ሞት ደኑ
መተቃቀፍ መርጠው ማማና ወይን ኾኑ

* * *



ይችላል ይሉኻል ፍልሚያ ማዘጋጀት
ያባት አጥንት ወስዶ ስሎ ጦር ማበጀት
አንተው ጦር ወርውረኽ አንተው ቀድመኽ ወደቅኽ
አካሌ ደረቱ መኽንኽን መች አወቅኽ?!

# ፍካሬ እውነት

“ሰማዩ!
እንዲህ እንደዛሬ ርቆ ሳይወረወር
ሁሉ ‘ንዳሻው የሚቆርሰው
ሁሉ ‘ንዳሻው የሚጎርሰው
ግዙፍ እንጀራ ነበር”
ብለሽ የነገርሽኝን እውነት ነው ተቀብያለኹ
ምክንያቱም ወድሻለኹ

“እያቴ!
ሦስት መቶ ዓመታት ኖሩ
የመቶ ዓመት ሰው እያሉ
ብርቱ ጽኑ ነበሩ
ዝሆን በጥፊ ጣሉ
አንድ ጥይት ተኩሰው ሦስት ነብሮች ገደሉ”
ብለሽ የነገርሽኝን እውነት ነው ተቀብያለኹ
ምክንያቱም ወድሻለኹ

“አባቴ!
ከሰዎች ሁሉ ይለያል



ባይኖቹ ብቻ ባይኾን በማጅራቱም ያያል
ብለሽ የነገርሽኝን እውነት ነው ተቀብያለኹ
ምክንያቱም ‘ወድሻለኹ
ግና ጅል እንዳልመስልሽ አይደለሁም ተላላ
በርግጥ በጄ ብላሽለች ነፍሴ ሁሉን ተቀብላ
እውነት ማለት ከሚወዱት መስማማት’ንጂ
አይደለምና ሌላ።

# ተአምረኛው አባ

ለምድረ በዳይቱ አገራቸው
ሽፍታ ላስቸገረው ሕዝባቸው
ሲጸልዩ ሲሰግዱ
ሲማልሉ ሲማልዱ
አባ ተኝተው መሬት
በ'ንባ በሳግ በምሬት

"ጌታ ሆይ
አገሬን 'ባክህ አጽናናት
ከቀማኞች አድናት"
በማለት አርባ ዓመት ሙሉ
ኪራላይሶ ስማኝ ሲሉ
እሱም ተልቡ በማድመጡ
ቀማኞች ከሕዝቡ ወጡ
እናም ከጊዜ በኋላ
የመናኙ ያ'ባ ገላ
ተለውጦ እንደ ዘበት
ግዙፍ ጫካ በቀለበት
አባም ይህን ታምር ቢያዩ
እንዲህ በለው ጸለዩ



"ጌታ ሆይ
እነሆ የኔ ብዕዕና
ይኸውልህ ዛሬ ገና
ቀማኞችን ከሕዝብህ
አውጥቶ አስኮበለለ
ከመሬታችን ተሸሉ
ገላዬም ደን አበቀለ
ከቀባሀቸው ጣድቃን መሀል
እኔን 'ሚያክል ማን አለ?"
በታብዮ ይህን ብለው
ምልጃቸውን ሲዘጉ
ከሕዝብ የሸሹ ሽፍቶች
መጥተው እየተንጋጉ
ጀርባቸው ላይ ባለው ደን ውስጥ
ጥልቅ ብለው ተሸሸጉ!።

# መለየት

የለም! የለም!
መለየት ሞት አይደለም
ሞትም መለየትን አያከሰው
መለየትም ሞትን አይመስለው
ትርጓሜያቸው ለየቅል ነው
አንቺም እኔም ጅረት ኾነን
ከራሳችን ምንጭ ፈልቀን
በራሳችን ፈለግ ፈስሰን
ሕይወት በሚሉት መቅበዝበዝ!
አገር ምድሩን አዳርሰን
ሄደን! ሄደን! ሄደን! ሄደን!
ወርደን! ወርደን! ወርደን! ወርደን!
ሞት በሚሉት ውቅያኖስ
አንድ ስንኾን ተዋሕደን
ተገናኘን እንበል'ንጂ መች ጨርሰን ተለያየን
የለም! የለም!
መራቅ መለየት አይደለም
ሰው በሰዎች ግዞት
ችግር መከራ ይዞት
አገር ቀዬውን ጥሎ



# የነቢይ ህልውና

ትላንት
"ነቢይ ባ'ገሩ አይከበርም"

ዛሬ
ነቢይ ባ'ገሩ አይኖርም

ነገ
ነቢይ አይፈጠርም::

ስልቻውን በጫንቃው አዝሎ
ቅሉን ጨርቁን እንጠልጥሎ
ብቻውን ሄደ ቢለው ስፈርተኛው ተጻጽሎ
እርሱ በልቡ ሕንፃ በማይዘመው በማይፈርስው
ከተጓዘ አኑሮ ሰው
እውን ይኼ መለየት ነው?
የለም! የለም!
መለየት ይህ አይደለም
ትርጓሜያቸውን እንቀይረው
ላንቺና ለኔ ሌላ ነው
ከፊቴ ቁጭ ብለሽ
ከፊትሽ ቁጭ ብዬ
ክንድሽን ካንገቴ ጥለሽ
ክንዴን ካንገትሽ ጥዬ
የምታወሪው ሳይገባኝ
ራሴን ሳነቃንቅ
የማወራሽ ሳይገባሽ
ለይስሙላ ጥርስሽ ሲሥቅ
ቻው ቻው ሲለኝ ቀልብሽ
ደኅና ኹኚ ሲልሽ ዐይኔ
መለየት ይህ ነው ለኔ።



# በር እና ሽንቁር

የፍላጎት ቤቱ፣ የምኞት ማደሪያው
እያደር ሲለጠጥ፣ ግድግዳና ጣሪያው
ኗሪው ገላው ሰፋ፣ ጎጆውም ገዘፈ
ለበር የታሰበው፣ ሽንቁር ኾኖ ዐረፈ።

## ባለ አንካሳ ልብ ሯጭ

ቅልጥም ለማደንደን ቅቤ ከምትጠጡ
ጋሬጣን ለማምለጥ ጫማ ከምትመርጡ
የልብ ወጌሻ አምጡ፣
አንካሳ ልብ ያለው ምን በእግሩ ቢሮጥም
ቢያባርር አይዝም ቢሸሽ አያመልጥም፡፡

# የለንበትም

ልብህ የወዳጅ፣ ልብስህ የጠላት
በምን እንለይህ፣ በምን ብልሀት
መሳይ ልብስንጂ፣ መሳይ ልቡና
ለይተን ማወቅ፣ እንችልምና
ድንገት አግኝተን ብንገድልኽ የትም
የለንበትም! የለህበትም!

# መሸቷል አትበል

በውድቀቱ አትከፋ
በጎሕ መቅደድ አትጽናና
ብርሃንን ለመመጽወት
ወደ ፀሐይ አትበል ቀና
የኛ ፀሐይ ሐሩሯ'ንጂ ብርሃን አትወልድምና፡፡
"መሸቷል" አትበል ጀንበር ስትጠልቅ
ከዛጎሏ ውስጥ ገብታ
«መሸቷል» አትበል ፀሐይ ስትሞት
በከዋክብት ተተክታ
በውስጥህ ላለው ብርሃን
ግርዶሽ የኾንህ ለ'ታ
ያን ጊዜ ኾኗል ጽልመት
ያን ጊዜ ኾኗል ማታ፡፡

## የሰው ልክ

የሰው ልጅ ሁለት መደብ አለው
አንደኛ፦ የጨቀየ ገላ አድፎ የተጣለው
የመንጻት ተስፋ ያለው
ሁለተኛ፦ ዕድፍ ኾኖ ሳለ እንዶድ ነኝ የሚለው።



## ይድረስ ላድርባይ ጓዴ

እየለየ ጊዜ ቦታ እየመረጠ
እስስታማ መልክህ ገጽኽ ተለወጠ
አሀያ 'ንዳልነበርህ በሰርዶዎች መሀል
አህዮች ሲበዙ ዛሬ ጅብ ኾነሀል።

## ዕረፍቴን እሥሣለሁ

ሕዋሳት ተኝተው፣ ጡንቻች እንቀላፍተው፣ ዐይኖቼ ተዘግተው
'ልቤ ብቻ ነቅቷል' ግልቢያውን ሳያቆም - መባተሉን ሳይተው
እንደባተሌ ሴት - መጅ እንደምትገፋ - እንዳለባት ፃማ
ጓያዋን ስትከኩ የምታንጎራጉር - በሚያጽናና ዜማ
እሱም እንዲጽናና - ጅማቱ እንዲዝናና - ምጥን ስንኝ ፈጥሮ
በዜማ አቀናጅቶ - በወግ አቀናብሮ - አስማምቶ ለጀሮ
ራሱን ያደምጣል - እንደዚህ እያለ - ለራሱ እንጉራጉሮ

*　　*　　*

ልክ እንደ መናፈቅ - ቀኖና እንደ ጣሰ - እምነት እንደ ካደ
ከቀኖች ስልፍ ውስጥ - ማን ገዝቶ ለየው - ሰንበት ወዴት ሄደ?
ዕረፍት የት ገደመ - ወዴት ተሰደደ?

*　　*　　*

ጥንቸሉ ሐሳቤ - ንስሩ የቀን ሕልሜ
ከዔሊው ቅልጥሜ - ከሜዉሌቱ አቅሜ
ያላቻ ተጋጥመው - ሰርክ ሲፎካከሩ
ያለመዳረሻ - ያለጽኑ ወደብ - ሲያባዝኑኝ ኖሩ።

*　　*　　*



## ጋርዮሽ

ሕልም አለህ ይላሉ
ራእይ ያዘለ
ኮከብ አለህ አሉ
ትንቢት የታደለ
ሕልምህን ንገረኝ
ኮከብህን አሳየኝ
ተርጉሜው ልጽናና
መነሻዬን ልወቅ መድረሻዬን ላጥና
ባ'ንተ ዕጣ ፈንታ ውስጥ ርስት አለኝና።

አሳርፉኝ ብዬ - የተጠጋኋቸው ኾነውኝ የ'ረፍት ጠር
ጫንቃ እንዳለኝ አይተው - «ጫንቃ ያለው መጣ - ኑ ሸክም
እንፍጠር» ብለው በመናገር
ዛፎች እንኳን አልቀው - ከመስኩ ከሸጡ - ጠፍቶ ሳለ የ'ንጨት
ዘር
መከዳዬን ፈልጠው - ምርኩዜንም ጠርበው - አበጁልኝ ቀንበር

*                    *                    *

አትላስ የግሪኩ - አትላስ መለኮቱ - ምድርን ስላዘለ
ሲዘከር ጉብዝናው - ሲወደስ መጠሪያው - ጽኑ እየተባለ
የ'ኔ ሥሥ ትከሻስ - ምን ተብሎ ይጠራ
ተሸክሞ 'ሚኖር - ምድርን ካ'ትላስ ጋራ

*                    *                    *

ወዮ ለ'ኔ ገላ - ላልተደላደለ - ላልተ፟ላገለ
በቀን ለባተለ - ጡንቻው የኳሰለ - ጅማቱ የዛለ
በኀሊናው ጠፈር - በእጁ ወዝ አልባ አፈር - ሲቆፍር የዋለ
ሲመሽ - ጀንበር ስትሸሽ - የዕረፍትን መልክ ሊያይ
ተጋድሞ ሲያሥሣት - ከቡልኮው በታች - ከመደቡ በላይ
እንቅልፍስ መች ታምኖ - እኩይ ምትኅት ኾኖ
ክረምትና መፀው - በጋ መከር ብሎ - ሌሊቱን ሸንሽኖ
እርፍ እያስጨበጠ - ሁዳድ እየሰጠ- በላብ እያስዋኘው
በሕልም አሳርሶ - በሕልም አዘርቶ - ያለ ፍሬ ሸኘው፡



# ምሕረትህን መልበሴን

“ባዝኖ! ባዝኖ! ባዝኖ!
ዋትቶ! ዋትቶ! ዋትቶ!
በጭጋጋማው ቀን
በደመናው ሞቶ
'ርቃኑን ተቀብሯል”
ብለው ያወራሉ
ም'ረትኽን መልበሴን
የማያውቁ ሁሉ፡፡

## ለብርሃኖች

አንተ ጧፍ ነኝ ብለኸኝ
አምኜኽ
እኔ መቅረዝ ነኝ ብዬህ
አቅፌኽ
“ጽልመት ጉድ ፈላበት ዛሬ!”
በማለት እኔ ፎክሬ
አብረኸኝ ሸልለህ አንተም
«የብርሃን ብቸኛ ምንጭ»
መሰኘትን በማለም
ከኖርንበት ጥጋጥግ
ከከረምንበት የጎጆ ዓለም
ብንወጣ ተንደርድረን
ያልጠበቅነው ት'ይንት ቆየን
አገር ሁሉ ፀሐይ ኾኖ
እየሣቀ ቁልቁል ዐየን።



## የፍጻሜ ልዑል

በገፍ እየጠጣ - ወንዝ እና ዝናሙን
ባሕሩ ካልረካ
በጅምላ እያቀፈ - ፀሐይ ከዋክብቱን
ጠፈሩ ካልፈካ
በቀረብነው ቁጥር ግባችን ከራቀ
የተጀመረ'ንጂ ባይኖረን ያለቀ
ጣዕመ ህላዌ እንዳይኾን መራራ
ቅስም እንዲያንሠራራ
መሀላችን ካለ
ባለብዙ ጅምር ባለ ሺሕ ሙከራ
“የፍጻሜ ልዑል” ተብሎ ይጠራ።

# የሁለት ዘመን ሰዎች

ሲያቀብጠኝ
እርስዎን ዐይቼ
ያ'ካል ድክመትዎን
የመንፈስ ድቀቶን
ከልብ ተረድቼ
ምናልባት ምናልባት
'ርስዎ የእኔ አባት
ዋናው ችግርዎ
ከመሰሎችዎ
ካ'ረጋውያን ጋራ
መዋል ማደርዎ
መኾኑን ገምቼ
የመንፈስን ንቃት
የአካልን ብቃት
ዳግም እንዲቀስሙ
በ'ድሜ ከማንስዎ ከ'ኔጋ ይክረሙ
ብዬ ጋበዝ'ኩዎት እርስዎም እሺ አሉ
አዳርዎን አደርኹ አዋዋሌን ዋሉ
ወግዎን ተካፈልኹ ወጌን ተካፈሉ
'ሚበሉትን በላኹ 'ምበላውን በሉ



ይህን ባ'ረግ ግና
እርስዎ የ'ኔ አባት
ልክ እንደገመትኹት
መች ወጣት ኾኑና
ይልቅ አጋቡብኝ የ'ርስዎን አርጅና::

## ሰው አለ

ውሻው ዲዮጋንን እዩት ተጃጅሎ
በከንቱ ይጮኻል፣ "ሰው የት አለ?" ብሎ
ሰው ሠራሹን ፀሐይ በጣቱ እንጠልጥሎ።



## አመሻሽ ላይ

እንፋሎት ይመስል
ዕድሜው ሽቅብ ሄደ
አቅሙ ጅረት ኾነ
ወደ ታች ወረደ
የጥርሶቹ ንጣት
ሸሸ ወደ ፀጉሩ
በፀጉሮቹ ምትክ
ጥርሶቹ ጠቆሩ
እሱና ፈገግታ ተቆራርጠው ቀሩ።
ዕድሜ ራሱ አርጅቶ
ተዝለፍልፎ ዘምሞ
ተመርኮዘበት
ወገቡን ቆልምሞ
ሣቅልን አትበሉት
ሣቅ አያውቅም ጥርሱ
ሰው ካ'ረጀ ወዲያ
በገና ናት ነፍሱ
ለሚነካካው ጣት
ወዮታ ነው መልሱ።

## ፍኖተ አርነት - ፩

ተበዳይ መናፍስት
ታፍነው የኖሩ
ወደ አርነት ዐውድ በድንገት ሲጠሩ
ያስጠባቂ ዘብ ተከፍቶ ሳል በሩ
የገቡ አይመስላቸው ቅጽሩን ካልሰበሩ



## ድርሻዬን

ጠባቂ እንደሌለው
ከፋን እልባ ቀና
ከፍት ኾኜ ቢያገኘኝ
እጄን ሰደደና
ከቀኙ
ከሌቱ
እየቆነጠረ
ከ'ድሜው ጋራ ደርቦ
የ'ኔን ድርሻ ኖረ።

## ፍኖተ አርነት - ፪

ክቡር መንፈሴ ሆይ!
አንተው ሕግ አርቃቂ
አንተው ፍርድ አጽዳቂ
የውኅኒው ባለቤት
የውኅኒው ጠባቂ
ደካማው ሰለባህ
በኀይልህ ሥር ታስሮ
ያመልጥ ይኾን ሰብሮ
ይበቀለኝ ዞሮ
ምን ያስብ ምን ያቅድ
ምን ይክብ ምን ይንድ?
ብለህ በማውጠንጠን ዕረፍት ከምታጣ
ምርኮኛኽን ፈትሕ አንተው ነጻ ውጣ::



## ፍካሬ ህልውና

ውስጤ ሰፊ አገር ነው
በጋ የሌለበት
ጥቢ የሌለበት
ዓመት ሙሉ ካፊያ ዓመት ሙሉ ክረምት
ጭጋጉ ሳይሟሟ ዳዋው ሳይነቀል
ጀንበር የት ላይ ትታይ አደይ ምን ላይ ትብቀል?

* *

ምንም ሥልጣን የለው ጊዜ በ'ኔ ገላ
ስም ነው ለውጥ አይደለም "ቅድም" "አሁን" "ኋላ"
"ሐዲስ" ያልኹት "ትላንት" ሲሻግት ከታየ
የማላውቀው "ነገ"ም ካለፈበት ቆየ

* *

ከ'ናቴ
ካባቴ
ከወንድም ከ'ኅቴ
ከወዳጅ ጠላቴ
የ'ንባ ጠብ ሰብስቤ
ሽቅብ ደራርቤ
የሠራኹት ሕንፃ መቼም አልፈረሰ

'ሚፈርስም አይመስለኝ «ምጽአት» ካልደረሰ

*    *

ወገኛው አባቴ በወገኛ አንደበት
"ወንድ ብቻውን ነው የሚያለቅስ" በማለት
ይቀኝ ነበር አሉ፡፡
ዋ ድሮ! ዋ ድሮ! ቀረኹ ያ ሁሉ
እንባ ታማኝ ኾኖ የሚታዘዝበት
ያ'ባት ቅኔና ቀን አልፏል እንደ ዘበት
ባ'ደባባይ ኾኗል! የ'ኛ ብኩን እንባ
አይቆይም ታግሶ ከ'ልፍኝ እስክንገባ፡፡



# ከዛፍ የተቀሰመ ዜማ

ካ'ለም እቅፍ ወጥቶ
ካ'ለም እቅፍ ሸሽቶ
ወደ ገዳም ሲሄድ
ደክሞት ተዝለፍልፎ
ብላቴናው ያሬድ ካ'ንድ ዛፍ ሥር ዐርፎ
ከዛፉ ግንድ ሥር ትል ሲሸልል ሰማ
እንዲህ በሚል ዜማ
«ዛፉ ነው ሕይወቴ
ቅጠሏም እራቴ
ሰባት ጊዜ ልውደቅ
ሰባቴ እንድወጣ
የኋላ ኋላ 'ራቴን አላጣ»
ይህን ስትሰማ ቅጠሊቱ ራደች
መሸሸ ባይኾንላት ሙሾን አወረደች
«ዛፉ ሕይወቴ ነው
ግን ኀያል ቢመስልም
ተራራ ቢያክልም
የማታ የማታ
ከትል አያስጥልም»
ያሬድ ይኼን ሰምቶ

ትሉ በጥረቱ ራት ሲበላ አይቶ
ተስፋውን አጸናው
በቅጠሏ ዕጣ ግን ተነካ ልቡናው
ከዚያም ተመልሶ
የትሉን ፋክራ
የቅጠሏን ለቅሶ
ባንድ ላይ ለውሶ
ዜማውን ቀመረ
ዜማው ተዘመረ
ከሰው ነፍስ ተስማማ
በሰው ድምፅ አማረ።



## የመጻተኛው አገር

አገር ድንኳን ትኹን
ጠቅልዬ የማገዝላት
ስገፋ እንድነቅላት
ስረጋ እንድተክላት

## አልቦ ብሕትውና

ለካስ ብሕትውና ብቻነት አይደለም
የለም ብቻ መኾን ብቸኝነት የለም
ባ'ለም ውስጥ እያለ ወዳጆች ከበቡት
ካ'ለም ተነጠለ መላእክት አጀቡት
ከመላእክት ሲርቅ አጋንንት ቀረቡት።





በነፍሴ ሰማይ ላይ
ቢሠርቅ ጣምራ ፀሐይ
እንዱን ጋርጃለሁ
ሌላው ደምቆ እንዲታይ

## ባዶ ድስት

ሌሊቱ ይነጉዳል!
እሳቱ ይነዳል
አልበዘነም ጣቱ
ጊዜ እና ጭራሮን አፍሶ ይማግዳል
ባዶ ድስቱን ልጣድ ባዶ ለማገንፈል
ከንፍገት ይሻላል ዕጦትን ማካፈል፡፡



## ሕያው ዛፍ

ከጥንት እስከ ዛሬ
ሰው ተብሎ 'ሚጠራ ይኼ ሁሉ ፍሬ
ሰው ነኝ ብሎ 'ሚያምን ይኼ ሁሉ ቅጠል
በህላዌ ዛፍ ላይ ጠዋት ቢንጠለጠል
ተሲዓት በኋላ ይረግፋል እንደ ጠል
ከጥንት እስከ ዛሬ
እየተነጠሉ ከየቅርንጫፉ
በተራ በተራ ቅጥያዎች ሲያልፉ
አይደርቅም አይወድቅም
ሁሌም ያው ነው ዛፉ፡፡

# የባይተዋር ገድል

በቁም መስተዋት ፊት መቆምኽ ሲጨንቅህ
የቁም መስተዋቱ፣ «ሰውነትህ የታል?» ብሎ ሲጠይቅህ
ግድግዳው ላይ ያለች፣ የገደል ማሚቶ፣ ዝም ማለት ፈርታ
ሳሎንህን ስትሞላው ዝምህን አባዝታ
ሕልም የቀላቀለ፣ የዝናም ነጠብጣብ፣ ጣራኽን ሲመታ
ከመስኮትኽ ማዶ፣ የሌሊት ወፍ ሞታ
የጊዜ ስውር ክንድ
የጓሮህን ዋርካ ያላጋር ሲያስቀረው
በሌሊት ወፍ ምትክ፣ ክንፍ ያወጣ ሌሊት፣ ጎጆህን ሲዞረው
መረሳት የሚሉት፣ የኑሮ ገባር ወንዝ፣ አልጋህን ሲገምሰው
«መንሳፈፉስ ይቅር፣ መስጠም ያቅተዋል ሰው?»
ሲያስኝህ ዕድልህ
ያኔ ይጀምራል፣ የባይተዋር ገድልህ::



# ዳዊት እና ጎልያድ

እግዜርና ዳዊት፣ አብረው ተቧደኑ
ብቻውን ታጠቀ፣ ጎልያድ ምስኪኑ
አንዳንዴ ተገዶ፣ ለሽንፈት ሲፈጠር
በጥቅሻ ይወድቃል፣ እንኳንስ በጠጠር::

# አጥብቆ ተመልካች

አይሽ አይሽና
አበባ ከንፈሯ
አበባ ከንፈሯ
ከንፈሯ እንዴት ያምራል!
እንኳን የ'ኔን ገላ ንቦችን ይጠራል
እያልኩ አስባለሁ
ከንፈርሽን እያለሁ::
አይሽ አይሽና
አይሽ አይሽና
አበባ ከንፈሯ
አበባ ከንፈሯ
ትንሽ አብጧል መሰል
ማነው የቀጠፋት?
ተስማ ነው'ንጂ መቼም ንብ አይነድፋት
እያልኩ አስባለሁ
ከንፈርሽን ዐያለሁ::

አይሽ አይሽና
አይሽ አይሽና
አይሽ አይሽና



አይደለም ከንፈሯ
ዐይኔ ነው ያበጠው
ዐይቶ ያታለለ
ከንፈሯን ያሳዩኝ ቅል እያሳከለ
እያልኩ አስባለሁ
ከንፈርሽን እያለሁ::

አይሽ አይሽና
አይሽ አይሽና
አይሽ አይሽና
አይሽ አይሽና
ዐይኔን እንቃለሁ
ከፊቴ የማየው
ከንፈር ይኹን ግንባር
እንዴት ብዬ ዐውቃለሁ?
እያልኩ አስባለሁ::

## ፍሬሙ

ፎቶዋ
የወጣትነቷ
ግድግዳው ላይ ያለ
በ'ኔና በ'ሷ ፊት የተንጠለጠለ
ስንቱን አሳሰበኝ

የሚያምሩት ዐይኖቿ
የሚያምሩት ጉንጮቿ
የሚያምሩት ጭኖቿ
አሉ አሁንም አምረው
በፍሬም ውስጥ ታጥረው::

አጠገቧ ሁኜ
ሶፋ ላይ ቁጭ ብላ
እርጅናዋን አቅፋ
ለጋነቷን ስቅላ
እኔም ተአምር ሳይ
«ነው» ሶፋ ላይ ኾና
«ነበር» ግድግዳ ላይ::



## ምንቸት እና ጋን

ይኑሩ እንጂ ባገር
በቀዬ በሰፈር
ኩሬ ሙሉ ውኃ፤ ምድጃ ሙሉ 'ሳት
ዳውላ ሙሉ አፈር
የምንቸቶች ስፍር መቶ በጋን ይለካል
ጋኖች እንኳ ቢያልቁ ሌላ አፈር ይጦካል::

እንዴ ውልታውን
እንዴ ትዝታውን
        እየተነተነ
እንዴ በቅልጥሙ
እንድዜ በሕልሙ
        እየተማመነ
ሕይወት ምን ቢወራጭ
        ከሳሉን መች አልፏል
ከግድግዳው ዘሎ፣ ከሶፋው ላይ ዐርፏል::
እግዜር ወንዝ ያወርዳል
ሴቶችን ያስረጃል::
ሰው ወንዝን ያቆማል፣ ካብ ድንጋይ ደርድሮ
ሰው ዕድሜን ያቆማል፣ በፍሬም ውስጥ አጥሮ::
ከፈጣሪ ይልቅ ፎቶ አንሺ ይራራል
ሲጋነታችንን ባለበት ያስቀራል::



# አቅጣጫዬ

ከቤቴ በስተግራ
ነበር የቆሻሻ ክምር
የማይፈለጉ ነገሮች ድምር::
«የት ነህ?» ብሎ ለሚጠይቀኝ
መኖሬን እነግር ነበር
ከቆሻሻው ክምር በስተቀኝ::
እና ያ ቆሻሻ ተራራ
የማይፈለጉ ነገሮች ድምር
ወደሚፈለገው ቤቴ ሲመራ
ቆዬ፣ ቆዬ፣ ቆዬና
አንድ የቆሻሻ ማጽጃ መኪና
ክምሩን አፍሶ ወሰደ
ወደማላውቀው አቅጣጫ
አቅጣጫዬን ይዞ ነጎደ::

## ሕይወት እና ሞት

ዕጣ ፈንታ
የምዕራብን ዋልታ
ከጠፈር ላይ ትፍቃለች፣
በምሥራቅ የወጣች ፀሐይ
በኄ ሞት ውስጥ ትጠልቃለች።



## መልክአ ሕይወት

ያንን ገለባ ልብ ከደጅ የወደቀው
«እድራሻህ ወዴት ነው?» ብለህ እትጠይቀው
የነገው ነፋስ ነው፤ መንገዱን የሚያውቀው።

# በር

አንኳኳ!
ይከፈትልሀል፤
ስትገባ
ሌላ በር ይጠብቅሃል፡፡
ሕይወት
እልፍኝዋ በዝቶ
እልፍኝዋ
በበር ተሞልቶ
የመኖር መፍትሔ ቃሉ
«ሲያንኳኩ መኖር ነው»ካሉ
አንኳኩተው ከሚያስከፍቱ፣
ከውጭ የቆሙ ተሻሉ፡፡

# ባለ ዕፀ መሰውር

ዕፀ መሰውርን፣ ከደብተራ አግኝቶ
ከሰው እንዲሰወር፣ ገላውን ቀብቶ
እንደ እግዜር ሳይታይ
በሚታይ ጎዳና
ወደ ባንክ ሄደና፣
በንቁ ዘበኛ በሚጠበቀው በር
አልፎ ገንዘብ ሲዘርፍ አይ;ታይም ነበር።
በዚህ ተደስቶ
ከዘላለም ቀንበር፤ ካ'ይን ነጻ ወጥቶ
ግና፣ ግና፣ ግና
ተመልካች ባይኖረው
ሆድ ነበረውና
እህል ወዳለበት በፍጥነት አቀና
ምግብ ቤት ሲገባ፣ ማንም አልታዘዘው፣
አይታይምና።

# በውብት አላምንም

በቀን መመላለስ የታክታት ሀሊይ

በሌት እስክትወጣ

በጥቢ መቀጠር የሰለቻት አደይ

በበጋ እስክትመጣ

በውብት አላምንም

ባለቅኔ አልኾንም።

ዋርካ ሽትብ ሄዶ

የርግብ ክንፍ በመውረስ

ርግብ ሥርን ስዶ

እስኪተክል ድረስ

በውብት አላምንም

ባለቅኔ አልኾንም።

ሠዓሊዎች ሁሉ

የቀስም ዘር ሁላ ከንቱ ነው እያሉ

ባየር ብራና ላይ በጭስ እስኪስሉ

በውብት አላምንም

ባለቅኔ አልኾንም።

# አባት እና ልጅ

«ጎዳናው ድንግል ነው፤ አሻራም የለበት
ከቀደሙት ወገን ማንም አልሄደበት»
ይላል እመንትቶ!
አባቱ ባለክንፍ መኾኑን ዘንግቶ።

# ወትሮ መለያየት

'ደኅና ኹኚ' እላለሁ
መሄጃ ሳይኖረኝ
ባ'ለም መኖር ማለት
የሺሕ መለዩቶች፣ ድምር እንደ ኾነ፣ ልቤ እየነገረኝ::
ማምሸት:- ከቀን መለያዬት
መንቃት:- እንቅልፍ መሰናበት
መሥራት:- ዕረፍትን መሸኘት
መኾኑን፣ ከጥንትም፣ ልቡናዬ ያውቃል
አልፋ ኦሜጋ ነው «ቻዎ» የሚሉት ቃል::
የቀደመ መልክሽ
የቀደመ ፍቅርሽ
የቀድሞ ጠባይሽ
ከ'ኔ እየተነሡ
ትተውኝ ሲፈልሱ
«ቻው» ብቻ ተረፈ
ሰው አንድ ጊዜ ቢሄድ፣ የሸኚ ልቡና፣ ምንኛ ባረፈ
ሺሕ ጊዜ ይሸኛል፣ በጥቂት፣ በጥቂት እየተሸረፈ::

የሚጨበጥ ሳይኖር፣ ጣቶችን ደርድሮ

ማነው የሚያላግጥ፣ በሰው ልጅ ተፈጥሮ

እንግዲህ ከሌለ፣ በልብም፣ በጣትም ጨብጦ ማስቀረት

የስም ለውጥ ናቸው፣ ፍቅር እና ወረት

ደጎና ኹኚ ሁሉ::

# ሱላዊነት

የጋራችን ዓለም

የጋራችን ሰማይ

የብቻችን ሕመም

የብቻችን ሥቃይ::

# ሐተታ ቢራቢሮ

እንት ጊዜ ቀናኹኝ፣ በዚያ ቢራቢሮ
ከእግዜር መዳፍ ቀድሞ፣ አበባዪቱን ፈጥሮ
እግሯን መንገድ ነስቶ፣ መሬት ላይ ተከለው
ከሳማት በኋላ፣ እንዳትከተለው፡፡

ሰው ብርቱ ነው፡፡
ዶፍ ነጎድጓድ መች ይፈራል
በጎርፍ ውስጥ
አረማመድ ያሳምራል፡፡
እኔ ግና
አማተብኹኝ ደንብሬ
በክረምት
መብረቅ ልቤ ላይ አስሬ

* * *

ካፍያው!
ካፍያው ፊቴን ቢመታው
እንባዬ!
እንባዬ ጠፋ ከቦታው
ላሳዝንሽ ...
እርሜን ዛሬ ልቅሶ ቢያምረኝ
ዝናሙ
ቀንቶ ተፎካከረኝ፡፡

* * *

ለክረምቴ!

ጋቢ ናት ስል ጃንጥላ

ተጓዘች ...

የጥቢን ቁልፍ አንጠልጥላ

እርሷ ፀሐይን ለብሳ

ለኔ ጭጋጉን ጥላ::

* * *

ጠቷ የታል?

ሽንጧ የታል?

ካፖርቷና ጎጆዋ

ውብ ገላዋን ስልቅጦታል::

* * *

ምድጃዬን!

እንዲህ ቆፍንና በርዷት

በገላቸው

እሳቴን ጭረው ወሰዷት

እሳቴ!

እሳቴ! እሳቴ! እሳቴ!

ተመለሽ ወደ ማጀቴ

ካፊያ ተነስንሶበት፣ ውኃ ኾኗል ሰውነቴ



* * *

ባላንጦቼ!

ኋላ ይዋረዳሉ

እሳቴን ሰርቀው ቢዘሩ

እሳተ ገሞራ ያጭዳሉ::

# ትቀሪያለሽ ብዬ

ስትዘገይ ጊዜ፣
ትቀሪያለሽ ብዬ

ከቃል፣ ከፈቃድሽ «መጣኹ» ብሎ መውጣት
«አትድረስ» ካልሽበት፣ ደረስ ብሎ መምጣት፣
ምን ይጎዳል ብዬ፤
የደፈረሰውን፣ ልቤን ሳላጠራው
ደረቴን በልክሽ፣ አፍርሼ ሳልሠራው
የተገለጠውን ሳላለባብሰው
የተሰደደውን መልኬን ሳልመልሰው፡፡
ትቀሪያለሽ ብዬ፤

ሐቅን «እክ»፣ ብሎ ከራስ መደራደር?
ወይ እውነት ተናግሮ፣ ሲፋለሙሽ ማደር?
የትኛው ነው 'ሚበልጥ?
የሚለውን ሳልመርጥ፡፡
ትቀሪያለሽ ብዬ
ተዘናግቼ ሳል፣
ከሺሕ ጥላ ከብዶ ድንገት ጥላሽ ታዬ፡፡



# አልወጣም ተራራ

አልወጣም ተራራ
ደመናን ልዳብስ
ቀስተ ደመናውን፣ ሽቅብ ልቀለብስ
አልዋስም እኔ
ካ'ቡን ተክሉ ክንፍ
ከያዕቆብ መሰላል
እኔ መውጣት ሳስብ
ሰማዩ ዝቅ ይላል፡፡

## ዋ.ሸ.ን.ት.

ሽንበቆ እንኳ
የነፋስ ክንፍ ሲነካካው
በስልት እንዳልደነሰ
የኛ ትንፋሽ ሲገባበት፣ ተንሰቅስቆ አለቀሰ::



## በድንቅ አብቃይ ምድር

አገሩ በሙሉ፣ የብስና ባሕሩ፣ ውኃ ሠራሽ ኾኖ
ላምን ያስቡታል? ዓባይን ለመስኖ
ለኛ አልተሰጠንም? ዓለምን መመልከት፣ ከጥቅሙ ነጥሎ
ውኃ ተሸምኖ፣ ባዬር ሲተጣጠፍ፣ ማዬት ዝም ብሎ
ሐሳብን ማሳረፍ፣ ከማር፣ ከሰም ስሌት
ለኛ አልተሰጠንም፣ ማዳመጥ፣ ማጣጣም፣ የንብን
ማሕሌት
ዶሮን ከዶሮ ወጥ ነጥሎ መመኘት
ለ'ሳት ቀለም ክንፉ፣ ለንጋት መዝሙሩ፣ ላጫጫር
ምስጢሩ፣ ቃል መርጦ መቀኘት
ፈልጠው፣ ሳይማግዱት ወይም ሳይዳስሱት፣ ከሥሩ
ሳይሰግዱ
ዋርካ አይደነቅም? በእንግዳ ህላዌው፣ በቅጠል በግንዱ?
መልስ የለም
መልስ የለም::
ከጢስ እና ውኃ የተሠራ ሸማ፣ ባዬር ይታጠፋል

# ዝማሬ

በሸንቁር ሰማይ ሥር፣ በስንጥቅ ምጣድ ላይ
ባ'ንድ ላይ ጠልቆባት፣ ጀንበር እና ሲሳይ
ምድጃው ሥር ኾና፣ ስትተክዝ ነፍሴ
ራት ኾና መጣ፣ የመሸበት ቁርሴ።



ንቡም ይዘምራል፣ ዶሮውም ይጭራል፣ ዋርካውም በእጆቹ
እየሩን ይቀዝፋል
የማይገርመው ትውልድ፣ በድንቅ አብቃይ ምድር፣
እየኖረ ያልፋል።

## ክልክል ነው!

*ማጨስ ክልክል ነው!*

*ማፏጨት ክልክል ነው!*

*መሽናት ክልክል ነው!*

ግድግዳው በሙሉ ተሠርቶ በክልክል

የቱ ነው ትክክል?

ትንሽ ግድግዳ እና ትንሽ ኀይል ባደለኝ

«መከልከል ክልክል ነው!» የሚል ትእዛዝ አለኝ፡፡



## ፈረቃ

ሞት እና ሰውነት ሁሌም ይነቃሉ

ነፍስ እና ነፋስ ግን ወቅት ይጠብቃሉ፡፡

ሁሌ ሕያው መኾን እስተመ በቃ

የኛ ሕያውነት ኾኗል በፈረቃ፡፡

# አደይ መነኮሰች

አደይ መነኮሰች፣
ከነማሃይ ዐይታ ቢጫዋን ለበሰች
ንቦች ኮበለሉ
ለመሥዋዕት ታጭቷል፣ ቁንጅና በሙሉ።።



# መልክአ ሕይወት

ሕዳኝ በንስሐ ስይፋ አልዶለዶመም
ታዳኝ በጸሎቱ ካ'ራጆች አልዳነም
ተኩዋሹ ቢዋልል አልመታ ቢል ተኩሱ
ካፈሙዝ ይጠጋል ዒላማው ራሱ።።

## የሌሊት ዜማዎች

ተዋነይ ነው አሉ!

ሞትን የገዘተ ሰባት ዓመት ሙሉ

ታዲያ ምን ይደንቃል?

እንቅልፍን ገዘትኹት እኔ በምስኪን ቃል፡፡

የዕድሜዎቼን እሹት

ቢበላ ቢበላ

አሲዳም እንቅልፌ መቼም ከርሱ አይሞላ

መደቤን አፍርሼ ከሕልሜ ልጣላ

*           *           *

ተዋነይ ስለምን እግዜርን ይከሳል

ሞት እንዴ ይመጣል! ሕልም ይመላለሳል

መቃብርን ደፍኖ ሞትን በቁም አስሮ

ሰው ነፍሱን ይቀብራል? ሕልሞቼን ቆፍሮ

*           *           *

ተዋነይ ምርኮህን ልቀቀው ይፈታ

ና! እንቅልፍን እንሰር በሞት እግሮች ፈንታ



## ያጮለቀ ብቻ

ጠቢብ ቤት ሳይኖረው፣ መስኮት ይከራያል

ግድግዳ ሳያቆም፣ ሽንቁር ይከራያል

ያጮለቀ ብቻ ሁሉን ነገር ያያል፡፡

ባልጋ እቅፍ ለኖረ ጉድጓድ መች ይከብዳል?
ከመቃብር ይልቅ ሕልም ይጎደጉዳል።

* *ተዋነይ በቅኔ ቤት አፈ ታሪክ ምትን በግዝት ለሰባት ዓመታት ያቆመ ጀግና ነው።*



# እርሷ እና እርሱ

ቅቤ ለደደላት፤ ቅሉን እንጠፍጥፎ
እንጀቷን እራሰው፤ እንጀቱን እጣጥፎ
ተቀባይ ሲወደድ፤ ሰጪ መች ይከስራል
እርሷ ለተቀባች፤ እርሱ ወዝቶ ያድራል።

# ፍግ ላይ የበቀለች አበባ

አበባዪቱም አለች፣
ፍግ ላይ የበቀለች
«ምንድን ነው ጥበቡ?»
ኔክታር ማጣፈጡ
አደይን ማስዋቡ፣
እኔም መለስኩላት፣
«ይብላኝ ለንብ እንጂ ዝንብማ ይተጋል
ከቆሻሻ ዓለም ውስጥ ጣ'ምን ይፈልጋል፡፡»



# ነጠብጣብ ሐሳቦች

ሰማይ ከሚመክን ይፀንስ መከራ
ያርግፍ! ያርግፍ! ያርግፍ! መአት እያፈራ
የ'ሳት ዛፍ ባለበት ሰደድ ላያስፈራ፡፡

* * *

ከሐምሌት ጋራ ሞቷል፣ የማመንታት ዓለም
ከኾኑ በኋላ፣ አለመኾን የለም!
ሸክም ጸጋ ኾኗል ጸጋህን አትግፋ
በጠባብ ዓለም ውስጥ ትከሻህን አስፋ፡፡

* * *

አንድ ሕልም እንደ ጠጅ፣ እየደጋገመ
ንግር፣ ትንቢት ሳይኾን ታሪክ እያለመ
ተኝቶ መነሣት
አቤት ሲያቅለሸልሽ
ጌታ ሆይ አትንሳት
ነፍሴን እንቆቅልሽ፡፡

## ገበያ

የሌሊት ወፍ ሲኾን፣ ሽማቹ በሞላ
ጨለማህን ሽጠህ፣ እንጀራህን ብላ::



## ለአለቃ ገብረ ሐና

(፩)

ቢታረክ ሁዳድ ላይ፣
ጠል እየወረደ፣ ወፍ ዘራሽ ሲያበቅል
ድፍን ኾኖ ሲያድግ፣ አገርም እንደ ቅል
ባለመታወቁ፣ መስኮት ወይ መውጫ በር
ለመውጣት መመኘት፣ መውጣት ማለት ነበር
ወላዋይ ሰማይን
አሻሚ አማርኛን፣ ታዝቦ የሣቀ
ከማመን ማመንታት፣ መሻሉን ያወቀ
ኮከብ መጥቶ ነበር፣ ከኮከብ የላቀ
ወሮቻችን ፀሐይ
ነገሥታቱ ፀሐይ
ቅዱሳኑ ፀሐይ
በፀሐይ መጥለቅለቅ፣ አገሩ ታምሶ
እንኳንስ መዓልቱ፣ ሌ'ቱ ብርሃን ለብሶ
ተወርዋሪ ኮከብ፣ ቀረ ተድበስብሶ

(፪)

ያለ መዳረሻ፣ ወደ መንገድ መውጣት
ዳንኪራ መጨፈር፣ አረቄ መጠጣት

ያለምንም ጥቅም - ፀሐይ ላይ መሰጣት
ያለምንም ምኽኛት - ከሴት ጋራ መተኛት
ታይተው እንደዋዛ
አይጠቀለሌው፣ ኑሮ ተጠቃሎ
መወለድ፣ መኖር መሞት፣ ላገር ነው ተብሎ
እንደ ሰም ለበስ ቃል፣
ፍቺው እያሻማ፣ አገር ባስቸገረ
የሞቱለት ሄዶ፣ ሞታቸው ከቀረ
ለካስ ያባቶች፣ faith ፣ ፌገዘ ብቻ ነበረ::

## (፫)

በታሪክ ሜዳ ላይ
አሉላ፣ ጎበና
ወንዱን አስከትለው ሲገድሉ፣ ሲሞቱ
አባ ገብረ ሐና
እርስዎ ባይኖሩ፣ ምን ይውጠው ሴቱ?

## (፬)

ጨመረልኹ መሰል፣ ባባ ነፍሶ ፈንታ
እንደ አንደበትዎ፣ እንትንዎ መንታ
አንዱ ለቀን ሲኾን፣ አንደኛው ለማታ



## (፭)

አሰግድ ልበልዎ፣ ስንቱን አሰገዱ
ወንዱን እና ሴቱን እያርበደበዱ::
Ass ሰግድ ልበልሁ ስንቱን Ass ሰገዱ
ሴቱን እና ሴቱን እያርበደ-በዱ::

# ጠፈር ሳስማምር

በገላ ጫካ ውስጥ፣ ገብቶ እንደ መሰወር
ተግቶ እንደ መባለግ፣
ቀኔን አባከንኩት፣ ቅኔ በመፈለግ::

*        *        *

ከስንኞች ይልቅ ትንኞች በለጡ
ጠፈር ሳስማምር
በሳሎኔ ትቢያ፣ መሙላቱን ገለጡ::



# ጠለሳ

የ'ሳቶችን እናት፣ ፀሐዩቱን ሸሽተው
ወፎች፣ ከብቶች፣ ሰዎች ከዛፍ ሥር ዐረፉ
የት ይጠለል ዛፉ?

## ሌላ ህላዌ አለ

ጋን ከጆርባ ወድቆ፣ ገል ኾኖ ቀጠለ
ከመሰበር ወዲያም ሌላ ህላዌ አለ፡፡



## ከተመኙ ላይቀር

ከተመኙ ላይቀር፣ ወንዝነት መመኘት
አገርን ሳይለቁ፣ ሌላ አገር መገኘት፡፡

## የግድግዳው ሰዓት

ግድግዳው ፈረሰ

የግድግዳው ሰዓት፣ በባዶ ታጠረ

የጊዜ ጠቋሚ

«ለኑሮ ሩብ ጉዳይ» እያለ ቆጠረ።



## የሥልጣኔ መዝሙር

ማንጋጠጥ እንድችል

«ደመናው የ'ኔ ነው!» እንድል

ተራሮችን እንድነድል

ከጥልቅ ሸለቆዎች ጥግ

የምንጭ ዱካ እንድፈልግ

ከሀኖስ ...

እስከ ውቅያኖስ

መንገዴን እንድዘረጋት

ልቤን እርካታ የለሽ

ሕይወቴንም ጥም አድርጋት።

## የልቤ ጸሎት

አቤቱ! አንተ ስም ሰጠኸን፣
እኛ ቅጽል ፈጠርን
አንተ ቤት ሰጠኸን፣
«እልፍኝ፣ ሳሎን» ጨመርን
ፊትህ ቢገሥጸን፣ ፊትህን እንዳናይ
ከምድር አንሥተን፣ ሰቀልንህ ከሰማይ።



## ከመኖር የሚሻል

ዳግም ተወለደ፣ የሞተው ደመና
የዘንድሮን ሥጋ፣ ለብሶ ወረደ አምና
ከመኖር የሚሻል፣ ምንም የለምና።

## ከአንድ ሯጭ ሐውልት ሥር የሚጻፍ ማስታወሻ

ተዘርቶ እና አፍርቶ
በቅሉ ከስሞ መቅረት
ሲኾን ተረት ተረት
የመቀያየር ሕግ፣ በህላዌ ሰፍኗል
ነፋስ የነበረ፣ ዛሬ ድንጋይ ኾኗል።

አየኹት! አይቼው፣ እንባ ባ'ይኔ ሞላ
ለካስ ካንድ ድንጋይ እንደ ላሊበላ
ትካዜም ይቆማል ተጠርቦ በመላ፡

ሲሮጥ አየው ነበር፣ ሲሮጥ በባዶ እግሩ
ከጠጠር ተዛምደው
ሥጋ ደምን ከደው
እግሮቹ ጠጠሩ።

ጠባዩን ያጋባል፣ ጎያሉ ለሚያንሰው
እናም ታላቅ አለት
ትንሽ ለኾነ ሰው
መርጋት አወረሰው።



## ውበት እና ጎጆ

ቀንዷ'ውጣ ሆይ!
ውብ ዛጎልህ አማለለኝ
ከጎጆህ ላስወጣህ ነው (ይቅር በለኝ)
'በዝግ ዓለም፣ ሰማይ ጣራ ነው' ይባላል።
ያለውበት ነው እንጂ ያለቤት መኖር ይቻላል።

# ዝግ ዓለም

ከትራሴ ግድም፣ በተደፋው ሰማይ

ኮከብ እያበራ፣ በመከዳዬ ላይ

ምንም አላነበብኩ፣ ከሕዋው ሰሌዳ

'እውነት እና ንጋት እያደር' እንግዳ

* * *

ግእዝ፣ አፈ እንግሊዝ

ልሳነ ፈረንሳይ

ትግርኛ አማርኛ

ወይም ኦሮምኛ

ቋንቋ በላይ በላይ፣

ደራርበናል ቢሉ

ከሌሊት ምስጢር ውጭ ሰዎች ምን ያውቃሉ?

የኅሕ ምስጢር ያለው፣ በዶሮ «አኩኩሉ»

* * *

በአዋሽ ሸለቆ

መቆፈሪያው አልቆ

ማን ያሳዩኝ ይኾን? ደጃፌን ቆፍሮ

የመግቢያ መውጫዬ፣ ምስጢሩ ተቀብሮ



# የአንድ ኢትዮጵያዊ ቴሌቪዥን አጭር የሕይወት ታሪክ

ቴሌቪዥኑ

ሰውዬውን ዐየው

ሰውዬው ያፈጣል

ሻጋታ መረጃ ባ'ይኑ ያላምጣል።

ዐይኑን ላፍታ ማርገብ ከሸንፈት ቆጥሮ

ያይኖቹን ሽፋሽፍት በችካል ወጥሮ

ባዶና ት'ይንቱን በቅጡ ሳይለዩው

ያፈጣል፣ ያፈጣል፣ ያፈጣል ሰውዬው።

እግዜሀር ደግ ነው

ዐይንን ባ'ምሥ'ል አምሳል ግንባር ላይ ቢተክልም

ሲያበሩበት ቢያድሩ ላይን አያስከፍልም።

ግን ቴሌቪዥኑ

ታካች የፈጠረው ታካች በመኾኑ

ለውጥ እየተመኘ

ክፍሉን ባ'ይኑ ቃኘ

ካፍጣጪ ሰው በቀር ምንም አላገኘ

ስለዚህ ሰለቸው፣ ታከተው ተከፋ

እኩለ ሌሊት ላይ ራሱን አጠፋ።

## መወለድ

ያንዲት ሌሊት ሽፍደት

የዘላለም ስደት

ለመጭው ያኖራል

ያባት ግዞተኛ «ልጅ» ተብሎ ይጠራል ::



## የ‘ኔ Copy Right

ተሰጥኦ ኖሯቸው፣ ዜማ የደረሱ

ዜማ ቢሰረቁ ለዳኛ ከሰሱ

እኔስ በተራዬ፣ የት ሄጄ ልክሰሰው

ዝምታዬን ሰርቆ ዝም የሚለውን ሰው::

## ሰም እና ወርቅ

በገላጣው ዘመን
ያዬ ከጨፈነ በማይተልቅበት
አንድ በኾነበት
ግልጡ እና ድብቁ
ሰሙ ገጽ አይደለም ሽክም ነው ለወርቁ።



## ጣዕምን ፍለጋ

ዋጋው ሲያጠራጥር ይኼ ፈራሽ ገላ
ሰውን የሚበላ
ጭራቅ ይውለድልኝ የኑሮዬ ተረት
ይጸጽታልና ሳይጣፍጡ መቅረት።

# ፈውስ

በክኒኑ ፈንታ

ቀለም እና ቃላት

ሐኪሞች ሲያድሉ

ሕመሙን ማስጌጥ ነው፣ የሰው ልጅ ዕድሉ።።



# እሳቱ ይነዳል

ይነዳል!

እሳቱ ይነዳል

ከዛፎች መቃብር፣ አመድ ይወለዳል።።

ይንኳኳል!

ይርዳል ጉበኔ

አዲሱ ሰው ገብቷል ልውጣ አሮጌው'ኔ

ከልጄ እትብት ጋር ተቋጥሯል ከፊኔ።።

## ለአንድ የአትክልት ቦታ

ችፍግ ያሉ ሣሮች
ያልተከረከሙ
ከደጃፌ በቅለው፣ ሐሳቤን ቀየሩት
ወደ ተስፋ መሩት::
ችፍግ ያሉ ሣሮች
ያልተከረከሙ
አረንጓዴ ኖሯል የተስፋ ቀለሙ::
ችፍግ ያሉ ሣሮች
ከመቼው ጠመቁኝ፣
ከመቼው ተወልደው
ካልኾነ በስተቀር፣ ከጠሉ ጋር ወርደው
ሥጋ ለብሶ ወርዶ
ሳያሳልፍልኝ፣ ዝም ብሎ ያለፈው
ሣር ለብሶ ተወልዶ
ሽክሜን አረገፈው::



## ግርዶሽ

ደመናው እንዴት ይታይ?
ሸፍኖት ሰንደቃላማው፣
ሸፍኖት ብሔራዊ መዝሙሩ
ብሔራዊ ልቅሶውን ማን ይሰማው?

## ለአንድ የአበባ እርሻ

አበባው ነው ማሳ

አበባው ነው አረም

ዓመቱን ጠቅልሉ ተኝቷል መስከረም

አበባ ያመርታል፣ ገበሬው በሙሉ

የጎመን ተስፈኞች ጽጌረዳ ብሉ::



## ነገረ ኮንዶም

ኮንዶም ግማሽ ችግር

ኮንዶም ግማሽ መላ

ኩቶም አያሻግር

ገላን ወደ ገላ

ድንግል ኾኖ ይቅር?

ሴት አውሉ ሁላ::

## አቤቱታዬ

ሜዳ አደረጉት ዳገቴን
ወዴት ላድርሰው ጉልበቴን?
ከሁሉ በላይ ሽንፈት
ያልተዘጋ በር መክፈት
'ባክህ ላክልኝ ፈተና
አቅሜን ይነግረኛልና፡፡



## ቅናት እና ሞት

መቼ ተወስኗል፣ ግርዶሽ ለጨረቃ
ሰሀሐይም አላት
        የደመና ጫንቃ
የሚሸፋፍናት
ለባለቅኔውም፣ አለው ባለቅናት

*        *        *

ቅናት እና ሞትን አንድ የሚያደርጋቸው
ጭንብል ሳይደርቡ፣ አለመምጣታቸው
ሞታችን ይመጣል
        የሌላውን ፍጥረት መልክ እየተዋሰ
ቅናት ይገለጣል
        የተፈጥሮ ፊቱን እያድበሰበሰ፡፡

# ሳንዲት የገጠር ሴት

ስትፈጭ የኖረች ሴት
መጁ በመጠኗ፣ ወፍጮውም በልኳ
ጓያ ትፈጫለች
ጓያ ሽሮ ሲኾን ያበቃል ታሪኳ።

አስባው አታውቅም
ወደ ኦናው ምድር ለምን እንደ መጣች
ከ'ለታት አንድ ቀን ከ'ናቷ ሆድ ወጣች
ከ'ለታት አንድ ቀን፣ ጡት አጕጠጐጠች
ከ'ለታት ሌላ ቀን ለባሏ ተሰጠች
ተዚያን ቀን ጀምራ
ተዚያን ቀን ጀምሮ
ድንግል ድንጋይ ወቅራ
ትፈጫለች ሽሮ።
አታውቅም፣
ማን እንደሚባሉ ጠቅላይ ምኒስትሩ
አታውቅም፣



ሹማምንት፣ በ'ሷ ስም፣ ምን እንደሚሠሩ
አነሣኹት'ንጂ እኔም ለነገሩ
በፖለቲክ ጥበብ ራስን ማራቀቅ
ምን ይጠቀማትና፣ ጓያዋን ለማድቀቅ።
ከቶ ማንም የለ፣ አበባ 'ሚሰጣት
ከቶ ማንም የለ፣ ከተማ 'ሚያወጣት
ከቶ ማንም የለ፣ በዳንኪራ መላ፣ ወገቧን የሚያቅፋት
ልፋቷም፣ ዕረፍቷም፣
ወደዚህ መጅ መሳብ
ወደዚያ መጅ መግፋት።
እንደ ዓባይ ፏፏቴ ሺሕ ዓመት ቢንጣለል
ቢጎርፍም ዱቄቱ
እንደ ሲኦል ወለል
ጫፍ የለውም ቋቱ።

ከዘመናት ባ'ንዱ
መስተዋት ፊት ቆማ፣ በተወለወለው
ፊቷን ለማዬት
ከፀጉሯ ላይ ያለው

## ግራገብ

ምድርን እንዳናስስ
ምጣድ እንደ ወጥመድ ከበበን
ኮከብ እንዳንቆጥር
ፈንድሻ ፈክቶ አናጠበን
በቅጡ እንዳንደምቅ፣ በቂ ጸዳል አለበስንም
በቅጡ እንዳንጨልም፣ ላ'ቅመ ግርዶሽ አልደረስንም
ተሩቅ ማዶ የሚመጣ «አይዞህ» እንኳ እንዳይተርፈን
ዕንቅፋትም ተጠየፈን::



ዱቄት ይኹን ሽበት ሲያቅታት መለየት
ያኔ ይገባታል የተሰጣት ዕጣ
ከማድቀቅ ቀጥሎ መድቀቅ እንደ መጣ::

የመጅ አገፋፏ - አምሳለ ሲሲፈስ
ከቋት ስስት እንጂ ሲሳይ አይታፈስ
ትቢያ 'ሚተነብይ፥ ዱቄት በዙሪያዋ
ከባርኔጣ አይሰፋም የኑሮ ጣሪያዋ
«ስትፈጭ የኖረች ሴት» ይህ ነው መጠሪያዋ::

ሲሲፈስ - በግሪክ ተረት ውስጥ የሚገኝ ተከናኝ ሲኾን
ኩነኔው ያለግብ ድንጋይ መግፋት ነው::

# የመሐከል ታሪክ

መላዕክትም አሉ፡-

«እጅግም ያልነጡ፣ እጅግ ያልከሰሉ
በርግብ ንጣትና፣ በቁራ ጥቅርሻ
መሐከል ላይ ያሉ
በማለዳ ጀንበር ምጣድ የበሰሉ
ቆንጆ! ቆንጆ! ቆንጆ ኢትዮጵያውያት አሉ»

ይህን የምኞት ቃል ተለዋውጠው ድንገት
ጠፈር ተከናንቦ እግዜር ከተኛበት
ካርያም ምኝታ
የክንፍም፣ የኮቴም ሳይፈጥሩ ኮሽታ
ቁልቁል ወደ ምድር ወርደው በዝግታ
ባውራ ዶሮ መላ፣ በሴቶች ላይ ወጡ
ክንፋቸው እንኪረግፍ
ዘራቸው እስኪጎርፍ - ገላቸውን ናጡ
በዚህ ሩካቤ፣ የተፀነሰው
ግማሽ ገላው መላክ፣ ግማሽ ገላው ሰው
ሰማይ ላይ አይተኛ፣ ይስበዋል ሥጋው
የብስ ላይ አይተኛ፣ በሰማይ ነው አልጋው
ሰማይም እንዳይቀር፣ ምድራቱም እንዳትቀር
ዕጣ ፈንታው ሆነ፣ ማንጋጠጥ ማቀርቀር።



# ለአንድ ጀግና

የጠብህን ጠበል ለሁሉ አታዳርሰው
ክንድህን አትዘዝ
ሰይፍህን አትምዘዝ
ሞቶ ለመጣ ሰው
የድመቶች ክብር
በሞታቸው ሰዓት
በነብር ወጥመድ ውስጥ
ተንደርድሮ መግባት
ለሐሳዊ ነብር ጦርህን አትነቅንቅ
በወጉ አያከብርም
በወጉ የማይንቅ።

# አንድ ክረምት፣ አንዲት ሴት

ጃንጥላ ዘርግታ
በጥቁር ብርጭቆ
ዐይኖቿን አግታ
ፊቷ ተደብቆ
ከፊል ተሸሽጋ፣ ከፊል ተከሥታ
ያቻት ዐያታለሁ::
ጥግ የለሽ፣ ጥግ ይዤ እየበሰበስኩኝ
ሰማይ የሸመነው፣ ውኃ 'ንደለበስኩኝ
ያቻት ዐያታለኹ
ያ ስመጥር ጡቷ፣ ከፊት እየመራት
ያ ስም አይጠሬዋ እየገፈተራት
ያቻት ዐያታለኹ
በብልጭታው፣ ሰበብ፣ ምስሏ ደምቆላት
በዝናም ነጠብጣብ፣ ፍሬም ተሠርቶላት
ያቻት ዐያታለኹ::
ከምበሰብሰው፣ ከ'ኔ በላይ ኹና
በጃንጥላዋ ልክ፣ ከሰማዩ ዘግና
ያቻት ዐያታለኹ::
ጃንጥላ፣ ሰባቂው፣ ክንዷ ሲንጠራራ



# መከራ ሲያልፍ

መከራ ሲያልፍ
ዝ-ም ብሎ መቼ ያልፋል
ገላችንን እንደ ምንጣፍ፣ ጎዳናው ላይ ያነጥፋል
ታለፈ በኋላ ተነሥተን፣ እንደ ጥንቱ ለመኾን ስንጥር፣
ጎናችንን ስንዳብስ፣
በጥንቱ ልክ አናገኘውም፣ ያ'ጥንታችንን ቁጥር
እመሬት ላይ አይታይም፣ የመከራ እግር ኮቴ
በግንባርህ መስመር ያልፋል፣ በ'ኔም አለ በማድያቴ
የፈላስፎች መርሐቸው፣ ለመረረን መች ጠቀመ
የመካሪዎች መብዛት፣ የመከራን ማየል ጠቆመ
ሰንበሌጥ አጎንብሶ፣ ቢያሳልፍም ነፋሱን
ሕይወቱን ቢያተርፍ እንኳ፣ ሠውቶታል ማጎንበሱን::

# አፈር እንቆቅልህ

አፈር፡-

በምድሬ ሥር፡- ማፍሪያ

በጥፍሬ ሥር ፡- ማፈሪያ

በውኃ የማባርረው

በደሜ የማስከብረው

በልቤ ስይዘው፣ የሚያሸልመኝ

በልብሴ ስይዘው የሚያስቀይመኝ፡፡



ካናቴራዋ አጥሮ

ዐይኔ ማዬት ትቶ፣ መገመት ጀምሮ

ከወገቧ ግድም፣ ምስጢረኛ አገልግል

ከወገቧ በታች፣ ቤርሙዳ ትሪያንግል

ይገኛል ስላለ

በውኃ ልብሴ ላይ፣ ግለት ተደረበ

ከሰውነቴ ላይ፣ ትነት አሻቀበ፡፡

# ለአባትየው

ወለደ፤

ወደ ኋላ ቀረ

በልጁ 'ርምጃ ልክ ይራመድ ጀመረ

ወለደ፤

ወደ ፊት ፈጠነ

እኔ በ'ኔ ስቀር እሱ ትውልድ ኾነ።

ወለደ፤

ብርሃን አረባ

ጨለማ ከመረ

በነበረው ሞት ላይ ሌላ ሞት ጨመረ።



# ማጽናኛ

የምትወጅውን ልብ

ደርድረሽ እንደ ጡብ

የሠራሽው ዓለም፣ ቢጋይም በ'ሳቱ

ከጉብ 'መዱ ላይ አይቀር መነሣቱ

ዐውቃለኹ

ታፈቅሪው ነበረ

ያፈቅርሽ ነበረ።

ግን ትልቁ ፍቅር

ትልልቁ ባሕር

ፀሐይም፣ ሰማይም

ሁሉም ባለጫፍ ነው፣ ጫፉ ባይታይም።

እንባ ቀንሺ'ንጂ አታልቅሽ አልልም

ዐውቃለኹ

ፍቅር በጠባዩ፣ እንዳስጨናቂ ሕልም

ለመግባት ነው'ንጂ ለመውጣት አይቀልም።

ሁለመናው ዓለም፣

ተንቀሳቃሽና አንቀሳቃሽ ኾኖ

ከነባረው ይልቅ ለበራረው መጥኖ

ዛፉ ከበረረ፣ ቅጠል ተመስሎ

ሐይቁ ከከነፈ፣ እንፋሎት ነኝ ብሎ

እያንዳንዱ ፍቅር፣ቋሚ የሚመስለው

ሸሽጎት የሚኖር ስውር አክናፍ አለው::



## ከዓለም ታሪክ የተዘለለ አንድ አንቀጽ

በ1994 ጫማዬ ተሸነቆረ

ለቀጣይ አራት ዓመታት

እንደ ተሸነቆረ ቀረ፤

ጫማ የተፋው እውራ ጣቴ፣ ውጋት ይሰማው ነበረ

ክሥተትን ሁሉ ጋረደ፣ ያውራ ጣቴ ትንሽ ሕመም

የጫማዬን ሽንቁር ያኽል፣ ጎድላ ታየችኝ ዓለም

ከእኔና ከእግር አምላኬ በቀር፣ ማንም ይህን አላስተዋለም፤

ሊቃውንት የዓለምን ክሥተት ሲጽፉ

የምድር ወገብ መስመር በሳሎኔ ባለማለፉ

መኖሬን ገደፉ፤

ሁሉም እንደ ፈቃዱ ቢመርጥ የታሪክ ርእስ

አንዱ በፈረንሳይ አብዮት ቀለም ቢጨርስ

አንዱ በግሪክ ቢጀምር

የዓለም ታሪክ አይሟላም የጫማዬን ሽንቁር ሳይጨምር::

# በደህንነት መኖር

በብዙ ጭንቅና በብዙ መከራ
አቁሜ ሲጃራ
እጠነቀቅ ብዬ፣ ለሳምባ፣ ለልቤ
በትምባሆ ምትክ ንፉግ አየር ስቤ
ከሱስ ፀዳሁ ልበል?
መኖርን የሚያክል ሱስ ተከናንቤ።

*           *         *

ከገነት ጋር ጠፍቶ የጤና ትርጉሙ
የተሻለው ህመም፣ ጤንነት ነው ስሙ
ግን አቅም አይጠፋም
አልጋ መነገጃ ለተሻለው ሰው
ወደ አልጋ መሄጃ፣ እጅግ ለባሰው።



# በነፃ መገምገምሮት

የበይ ተመልካቹ
ሲበሉ ስላዩ ምራቅ በመዋጡ
ተካፍሏል ከጎጆራው፣ ተካፍሏል ከወጡ
ተገምቷልና፣ በሂሳብ በዋጋ፣ ሁሉም በዚህ ዓለም
በነፃ መገምገምሮት ብሎ ነገር የለም

## ጤዛዊነት

ረጅም የሚሉት እንግዳ ፍካሬ

ለግዜሮች ነው'ንጂ ለሰው መች ታደለ

እኔም በፍጥረቴ፣ በድሜም በማጠሬ

እጭሩን ለጠጥኩት ረጅም መሰለ

*        *        *

አሸን ላ'ጭር ኑሮ

ክንፍ አለመለመ

እናም እዚያው በሮ

እዚያው ላይ ከሰመ

መኖሩ ባይኾነው

የዘላለም እቻ

በራሱ ገድል ነው

መብረር መቻል ብቻ።

*        *        *

ምንም ሳያሰጋት በትረ ብዙ ፀሐይ

ድንኳን ከዘረጋች ጤዛ በቅጠል ላይ



እያስፈልገኝም በግዜሮቹ መቅናት

ለኖረባትማ ማለዳም እድሜ ናት።

ጤዛዊነት፡- የዘልአለማዊነት ተቃራኒ የሆነ የግል አማርኛዬ ነው። ምናልባት እንግሊዘኛው transience ከሚለው ጋር አንድ ሳይኾን አይቀርም።

ጠለላ ........ 112
ጠፈር ሳስማማር ........ 113
ከተመኙ ሳይቀር ........ 114
ሌላ ህላዌ አለ ........ 115
የስልጣኔ መዝሙር ........ 116
የማድማዳው ሰዓት ........ 117
ከመኖር የሚሻል ........ 118
የልቤ ፀሎት ........ 119
ውበት እና ጉጀ ........ 120
ከአንድ ሯጭ ሐውልት ሥር የሚጻፍ ማስታወሻ ........ 121
ዝግ አለም ........ 122
የአንድ ኢትዮጵያዊ ቴሌቪዥርን ... 123
የ"ኔ Copy Right ........ 124
መወለድ ........ 125
ጣዕምን ፍለጋ ........ 126
ስምና ወርቅ ........ 127
እሳቱ ይነዳል ........ 128
ፈውስ ........ 129
ግርዶሽ ........ 130
ለአንድ የአትክልት ቦታ ........ 131
ነገረ ኮንዶም ........ 132
ለአንድ የአበባ እርሻ ........ 133
አቤቱታዬ ........ 134
ቅናትና ሞት ........ 135
ላንዲት የገጠር ሴት ........ 136
ግራገብ ........ 139
ለአንድ ጀግና ........ 140
የመሐከል ታሪክ ........ 141
መከራ ሲያልፍ ........ 142
አንድ ክረምት፣ አንዲት ሴት ........ 143
አፈር እንቆቅልህ ........ 145
ለአባትየው ........ 146





ማጽናኛ ........ 147
ከዓለም ታሪክ የተዘለለ አንድ እንቆጆ ........ 149
በነፃ መንቀሳቀስ ........ 150
በደህንነት መኖር ........ 151
ጤዛዊነት ........ 152
እውነት ስፈልግ ........ 154

(<u>ፈረ ልባ ጎጆዎች</u> ፣ <u>የሳት ዳር ሀሳቦች</u> እና
ሌሎች አዳዲስ ግጥሞች)

ሕትመት ፋር-ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ

ዋጋ 20 ብር